# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከጁን 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እና

## ከጁን 21-30/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጁን 2022
አዲስ አበባ

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከጁን 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ........ 3

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20 /2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ 4

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20 /2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ........ 5

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20 /2022 ድረስ የነበረው የዝና ብመጠን ........ 6

ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........ 6

እ.ኤ.አ ከጁን 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 7

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 7

እ.ኤ.አ ከጁን 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 8

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 8

እ.ኤ.አ ከጁን 21-30/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ ........ 9

እ.ኤ.አ ከጁን 21-30/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 10

እ.ኤ.አ ከጁን 21-30/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 11


# እ.ኤ.አ ከጁን 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አስር ቀናት ለክረምት ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ከዕለት ወደ ዕለት ተጠናክረዉ የተስተዋሉ ሲሆን፤ በተለይም በምዕራብና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ይበልጥ ከመጠናከራቸዉ ጋር በተያያዘ በቤንሻንጉል፣ በምዕራብ ኦሮሚያና ምዕራብ አማራ አንዳንድ ቦታዎች ላይ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ቅፅበታዊ ጎርፍ የማስከተል አቅም ያለዉና እስከ 135 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በተጨማሪም በምዕራብ ጎጃም ዞን በሰከላ ወረዳ እና በምዕራብ ሐረርጌ በጉሚ ቦርዶዴ ወረዳ ንፋስና በረዶ ቀላቅሎ የጣለዉ ዝናብ በንብረት እና በእንሰሳት ህይዎት ላይ ጉዳት ማድረሱን የተሰበሰቡ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይሁን እንጂ በየጣልቃዉ ፀሃያማ ሁኔታ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ተስተዉሏል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በምዕራብና መካከለኛዉ ኦሮሚያ፣ በቤንሻንጉል፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በሲዳማ፣ በጋምቤላ፣ በምዕራብ አማራ፣ በደቡብ ደጋማ ቦታዎችና ምስራቅ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡ ፡ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸው ጣቢያዎች መካከል አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያህል በነቀምቴ 135.0ና 50.2፣ በጊምቢ 53.6ና 52.3፣ በበደሌ 42.8ና 44.0፣ በአርጆ 38.5ና 64.5፣ በጎሬ 37.0፣ በሊሙ ገነት 36.2፣ በነጆ 46.5ና 48.4፣ በአሶሳ 53.2 እና በዳንግላ 35.5 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲነፃፀር በምዕራብ፣ መካከለኛዉና ሰሜን ምዕራብ ትግራይ፣ በምዕራብ፣ ደቡብ፣ መካከለኛዉና ሰሜን ጎንደር፣ በአዊ፣ በምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ በሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ በኢሉአባቦራ፣ በቡኖ በደሌ፣ በጅማ፣ በምዕራብና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ በቤንሻንጉል እና ጋምቤላ ክልሎች እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሁሉም ዞኖች፣ በጉራጌ፣ በስልጤ፣ በሀዲያ፣ በከምባታ እና ወላይታ ዞኖች ላይ ከ25-257 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ4-10 ለሚያህል ቀናት ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ የምስራቅና ደቡብ ትግራይ፣ የሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ(03)፣ የምስራቅና ሰሜን ሻዋ(04)፣ የአርሲና ምዕራብ አርሲ፣ የምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ ጥቂት የባሌና ምዕራብ ጉጂ፣ የደቡብ ኦሞ፣ የጋሞና ጎፋ፣ የሲዳማ ክልል ሁሉም ዞኖች፣ ከአፋር ክልል የዞን 04፣ 05፣ 02ና 03፣ ከሱማሌ ክልል የፋፈንና ሲቲ ዞኖች ላይ ከ5-25 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ4ላነሱ ቀናት ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2 (፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በምዕራብና ሰሜን ምዕራብ ትግራይ፣ በምዕራብ፣ ደቡብ፣ መካከለኛዉና ሰሜን ጎንደር፣ በአዊ፣ በምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ በሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ በኢሉ አባቦራ፣ በቡኖ በደሌ፣ በጅማ፣ በሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ በጥቂት የአርሲና ምዕራብ አርሲ፣ በምስራቅ ሐረርጌ፣ በፋፈንና ሲቲ፣ በአፋር ክልል ዞን 03፣ 01፣ 04ና 05፣ በቤንሻንጉል እና ጋምቤላ ክልሎች ሁሉም ዞኖች፣ በቤንች ሸኮ፣ በሸካና ከፋ፣ በጉራጌና በስልጤ ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 3) ፡፡


ካርታ 1   ኢ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20 /2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2    ኢ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20 /2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 3   እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20 /2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር




# እ.ኤ.አ ከጁን 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት የጁን ሁለተኛ አስር ቀናት ወደ ሀገራችን ይገባ የነበረዉ ዕርጥበት አዘል አየር በአብዛኛዎቹ ክረምት ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ተጠናክሮ የነበር ሲሆን፤ በተለይም በምዕራብና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ይበልጥ ከመጠናከራቸዉ ጋር በተያያዘ በቤንሻንጉል፣ በምዕራብ ኦሮሚያና ምዕራብ አማራ አንዳንድ ቦታዎች ላይ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ቅፅበታዊ ጎርፍ የማስከተል አቅም ያለዉና እስከ 135 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ የነበረዉ ዝናብ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማሻሻል አንፃር አስቀድመው የተዘሩና በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግም ሆነ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች፣ ለመኸር የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ፣ ለዘር፣ ለማሳ ዝግጅት እንዲሁም ለተለያዩ የቋሚ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች የውሀ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንፃር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረዉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአርብቶ አደርና በከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች የነበረው አንስተኛ የእርጥበት ሁኔታ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት አዎንታዊ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ እንዲሁም በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የነበረው ከባድ ዝናብ እንዲሁም ባሳለፍናቸው ቀናት በተከታታይ ዝናብ በማግኘት ላይ በነበሩ ቦታዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት የጎርፍ መከሰት የነበረ ቢሆንም፤ በግብርናዉ አንቅስቃሴ ላይ ያን ያህል ያደረሰ አሉታዊ ተፅዕኖ አልነበረም (ካርታ 4) ፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከጁን 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ከጁን 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ የተሻለ የእርጥበት መጠን በአብዛኛው አባይ፣ ተከዜ፣ ኦሞ ጊቤ ፣የላይኛውና የመካከለኛው ባሮ አኮቦ እንዲሁም በጥቂት በላይኛው አዋሽ እና ስምጥ ሸለቆ ከፍተኛ እርጥበት አግኝተዋል፡፡ በተጨማሪም በአብዛኛው የላይኛው ዋቤ ሸበሌ፣ የመካከለኛ አዋሽ፣ የላይኛው ባሮ አኮቦ፣ የላይኛው እና የታችኛው ስምጥ ሸለቆ ኪስ ቦታዎቻቸው ላይ ደግሞ መጠነኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ የተቀሩት አብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ከፊል ደረቅና ደረቅ ሁኔታ አመዝኖባቸው ተሰተውሏል (ካርታ 5) ፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




# እ.ኤ.አ ከጁን 21-30/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ የጁን ሶስተኛው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በይበልጥ እየተጠናከሩ የሚሄዱበትና ከዚህም ጋር ተያይዞ ሁሉንም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ ቦታዎችን የሚያዳርሱበት ጊዜ ነው፡፡

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የባህርና የከባቢ አየር ክስተቶች ከባለፉት ቀናት አኳይ በተለይም በመጀመሪያዎቹ የሳምቱ ቀናቶች ላይ እየተጠናከሩ ሊሄዱ እንደሚችሉና ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተለይም በምዕራብ አጋማሽና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ቡኖ በደሌ፣ የሰሜን፣ የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ የሸዋ ዞኖች፣ አርሲና ምዕራብ አርሲ ዞኖች፣ አዲስ አበባ ዙሪያ፣ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም፤ ሁሉም የጎንደር ዞኖች፣ የባህር ዳር ዙሪያ፣ አዊ፣ የሰሜን ሸዋ፤ ከትግራይ ክልሉ የሰሜን ምዕራብ፣ የምዕራብና የመካከለኛዉ ዞኖች፤ የጋምቤላ፤ የቤንሻንጉል፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እና የሲዳማ ዞኖች፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ከደቡባዊ የክልሉ አጋማሽ በስተቀር ሁሉም የክልሉ ዞኖች፣ በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበና አልፎ አልፎም በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ ከመደበኛ በላይ ዝናብ ያገኛሉ። በተጨማሪም ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በጥቂት ሥፍራዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ሊከሰት ይችላል። ከዚህም ሌላ ድሬዳዋና ሐረሪ፣ ምዕራብ እና ምሥራቅ ሐረርጌ፣ ዋግ ህምራ፣ ሰሜንና ደቡብ ወሎ እንዲሁም አጎራባች የአፋር ዞን 3 እና 5፤ ምስራቅና ደቡብ ምስራቅ ትግራይ በጥቂት ሥፍራዎቻቸው ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ሊያገኙ ይችላሉ። የተቀሩት የሀገሪቱ ዞኖች አልፎ አልፎ ከሚኖራቸው አነስተኛ የደመና ሽፋን በስተቀር በአብዛኛው ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጁን 21-30, 2022 የሚኖረዉ የዝናብ

## እ.ኤ.አ ከጁን 21-30/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

ከላይ በተሰጠው የአስር ቀን ትንበያ መሠረት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እየተጠናከሩ ሊሄዱ እንደሚችልና በተለይም በምዕራብ አጋማሽና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው እርጥበት ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይህም ሁኔታ በክረምት ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ለሚጠበቀው የግብርና እንቅስቃሴ ጥሩ ጎን እንደሚኖረዉ ይጠበቃል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በትንበያው ላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ የሚያገኙ ሲሆን፣ ከዚህም ጋር ተያይዞ የሚጠበቀው ዝናብ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማሻሻል አንፃር አስቀድመው የተዘሩና በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግም ሆነ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች እንዲሁም ለተለያዩ የቋሚ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች የውሀ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንፃር ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በአንፃሩ በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ በተለይም ባሳለፍናቸው ቀናት በተከታታይ ዝናብ በማግኘት ላይ በሚገኙ ቦታዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት እንዲሁም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ከአፈር መሸርሸርም ሆነ ከመሬት መንሸራተት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ሊያስከትል ስለሚችል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነዉ፡፡ በተጨማሪም በልግ አብቃይ በነበሩት አካባቢዎች ላይ የሚጠበቀው ዝናብ የደረሱ የበልግ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ተገቢዉን ጥንቃቄ በማድርግ በመካከል በሚገኙ ደረቅ ቀናት የሰብል ስብሰባ ተግባራትን ማከናወን ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የሚጠበቀው እርጥበት በመጠን ዝቅተኛ ቢሆንም፣ በተለይም ባሳለፍናቸው ቀናት አካባቢዎቹ ካገኙት የተሻለ እርጥበት ጋር ተዳምሮ የመጠጥ ውሀ አቅርቦትና የግጦሽ ሳር ልምላሜ ከማሻሻል አንጻር ጥሩ ጎን ይኖረዋል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ጥሩ አስተዋጽኦ እንደሚኖረዉ ይጠበቃል፡፡

## እ.ኤ.አ ከጁን 21-30/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የጁን ሁለተኛ አስር ቀናት የክረምት እርጥበት መፈጠር ሁኔታ በብዙዎቹ ተፋሰሶች ላይ እየተሰፋፋ እንደሚሄድና የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ የሆኑት ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት ሁኔታ እንደሚሰተዋል ይጠበቃል፡፡ ከነዚህም በአብዛኛው፣ አባይ፣ ኦሞጊቤ፣ ተከዜ፣ የላይኛው ገናሌዳዋ፣ ዋቢሸበሌ፣ የላይኛውና መካከለኛው አዋሽ፣ ስምጥሸለቆ እና ባሮአኮቦ ተፋሰሶች ከከፍተኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ከዚህም ጋር ተያይዞ በተጠቀሱት ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ ቦታዎችና ለጎርፍ ተጋላጭ አካባቢዎች ላይ ትኩረትና ክትትለል ያስፈልጋል። በተጨማሪም የታችኛዉ አዋሽ፣ የመካከለኛው ገናሌ ዳዋ፣ የአፋር ደናከል አዋሳኝ ከፍተኛ ቦታዎች በጥቂት ቦታዎች ላይ ከእርጥበታማ እስከ መጠነኛ ርጥበት እንደ ሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የእፅወት ሽፋን በሌለበት ገላጣ ቦታዎች እና ከተሞች ላይ አልፍ አልፎ ሊከሰት በሚችለዉ ከባድ ዝናብ ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊየስከትል ስለሚችል ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ አሰፈላጊ ነው። የተቀሩት የሀገሪቱ የደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ ተፋሰሶች ላይ ደረቅና ከፊል ደረቅ ሁኔታ ሰር እንደሚቆዩ ይጠበቃል። _